በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ.200480

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.......አቶ በድሩ አባገላን - ቀርበዋል

ተጠሪ፡............ የሟች አቶ አባድጋ አባጎጃም ወራሾች ወ/ሪት አልፋ አባድጋ አባጎጃም እና

አቶ ሀምዛ አባድጋ አባጎጃም- ወ/ት አልፍያ አግድጋ- ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የእርሻ መሬት ክርክር የተጀመረዉ በየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.14976 በ1/9/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ በሟች አባቴ አቶ አባገላን አባጊቤ እጅ ለ56 ዓመታት የቆየን ባህር ዛፍ ይዞታ ከዚህ ቀደም በመ.ቁ.09921 ላይ ባህር ዛፍ የሟች አባቴ ነዉ ተብሎ የተወሰነዉ የዉርስ ይዞታዬን በጉልበት ስለያዘብኝ የአሁን ተጠሪ ይዞታዉን እንዲለቅልኝ፣ የወደመዉን ንብረት ግምትና በክሱ ምክንያት የወጠዉን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ አመልካች ይህ መሬት በመ.ቁ.09921 ላይ ተወስኖልኝ በንብረት ክፍፍል አግኝቻለሁኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ሀሰት ነዉ፤ ይህን ይዞታ

ከደርግ መንግስት ጀምሮ ስንገብርበትና ለሶስት ዙር ያስለካን ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የአመልካችን የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ ከሚመለከተዉ አካል በማጣራት ባሳለፈዉ ዉሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነዉ የእርሻ መሬት የአሁን ተጠሪ አባት የአባጎጃም አባቂጤ መሆኑ እና በተጠሪ ወንድም በሚች አቶ አባጊዲ አባጎጃም ስም ግብር ሲገበር የቆየ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ በመ.ቁ.09921 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች አባት ከተጠሪ አባት ጋር በይዞታዉ ላይ ባህር ዛፍ በጋራ ተክለዉ ሲጠቀሙበት ስለነበር አመልካች መሐመድ አባጊዲ ላይ ክስ አቅርቦ የተወሰነዉ ባህር ዛፍ እንጂ ይዞታዉ አይደለም፣ አሁን ባህር ዛፉ ሸጠዉ ገንዘቡንስ የተካፈሉ ሆኖ ቦታዉ መንገድ ዳር ስለሆነ ጉቶዉ ደርቆ ተጠሪ እህል ዘርቶ የሚጠቀመዉ በመሆኑ፣ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ ይዞታዉን ለአመልካች የሚለቅበት እና ካሳ የሚከፍልበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም በየደረጃዉ ላሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች ቅሬታዉን ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ቅሬታዉን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር የወረዳዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ26/4/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአመልካች አባት በ1954 ዓ.ም ባህር ዛፍ ተክሎ እስከ 2000 ዓ.ም ሲጠቀምበት የቆየዉና በመ.ቁ.09921 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት በክፍፍል የባህር ዛፍ ይዞታ ለአመልካች ደርሶ እያለ እና ተጠሪ ይዞታዉን በጉልበት መያዙ ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ በጉልበት የተቀመሁት ባህር ዛፍ እንዲመለስልኝ የተጨፈጨፈዉ ባህር ዛፍ ግምት እንዲጠይቅ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ አስቀድሞ አመልካች በመ.ቁ.09921 ላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተከራክሮ ያስፈረደዉን ፍርድ በአግባቡ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት የተጠሪ ወራሾች ባቀረቡት መልስ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በማስረጃ በማጣራት የሰጡት ዉሳኔ ተገቢ ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት የመሬት ይዞታን የሚመለከት እና ተጠሪ ይህን መሬት በጉልበት ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ የሚል ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ረገድ ባቀረቡት ክርክር ለክርክር መነሻ የሆነዉ ይዞታ የአመልካች አባት ይዞታ ሳይሆን የሚች አቶ አባጎጃም አባቂጤ መሆኑን ገለጸዉ ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃን የመስማት የመመርመርና የመመዘን በሕግ የተሰጠዉን ስልጣን መሰረት በማድረግ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት ከሚመለከተዉ አካል ተጣርቶ እንዲቀርብ

በማድረግ ባሳለፈዉ ዉሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነዉ የእርሻ መሬት የሥር ተከሳሽ አባት የአቶ አባጎጃም አባቂጤ መሆኑን እና በሥር ተከሳሽ ወንድም ስም ተገቢ የመንግስት ግብር ሲከፈል እንደነበር መረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

በዚህ ይዞታ ላይ የሥር ተከሳሽ አባት አቶ አባጎጃም አባቂጤ እና የአሁን አመልካች አባት አባገላን አባጊቤ ባህር ዛፍ ተክለዉ ሲጠቀሙበት እንደነበር እና የአሁን አመልካች የዉርስ ይዞታን በተመለከተ በሌሎች ወራሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ መሐመድ አባጊዲ ላይ አሁን ለክርክር መነሻ በሆነዉ ይዞታዉ ላይ ያለዉን ባህር ዛፍ በተመለከተ ክስ ማቅረቡን የመ.ቁ.09921 ላይ የተደረገዉ ክርክር ያመለክታል፡፡ የየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.09921 ግራ ቀኙን በማከራከር በ15/6/2008 ዓ.ም ባሳለፈዉ ዉሳኔ አከራከሪዉን ባህር ዛፍ 7ኛ ተከሳሽ መሐመድ አባጊዲ ከአመልካች አባት ጋር የእኩል ነዉ በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ ዉሳኔ ይዘት መረዳት የሚቻለዉ ለአሁን አመልካች የተወሰነዉ ባህር ዛፍ እንጂ ባህር ዛፉ ያረፈበት ይዞታ እንዳልሆነ ነዉ፡፡

አሁን በተያዘዉ ክርክር ደግሞ የአመልካች አባት ባህር ዛፉን አብረዉ ከተከሉት ሰዉ ጋር ባህር ዛፍ ሸጠዉ ገንዘቡን የተካፈሉ መሆኑንና በአሁኑ ወቅት በይዞታዉ ላይ ጉቶዉ እንኳን ተነስቶ የሌለ መሆኑንና በመሬቱ ላይ እህል የተዘራ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ማለት ለክርክር መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ ቀድሞ የነበረዉ ባህር ዛፍ አሁን የሌለ እና ይዞታዉ ለእርሻ ሥራ እያዋለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ለአመልካች በመ.ቁ.09921 ላይ ተወስኖ የነበረው ባህር ዛፍ እንጂ የመሬት ይዞታ አይደለም፤ ባህር ዛፉም ቢሆን አሁን በይዞታዉ ላይ እንደሌላ የሥር ፍ/ቤቶች በማስረጃ አጣርተዉ ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡ አመልካች በኦሮሚያ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6 (1) መሰረት በዚህ ይዞታ ላይ የመሬት የባለይዞታነት መብት ያለዉ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የረጋገጠዉ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይህ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መፈጸማቸዉን የሚያመለክት ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን የገጠር መሬት ተጠሪ በጉልበት ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ በማለት ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.14976 በ1/9/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም